ከጠየቃችሁት የተሻለን ነገር አልጠቁማችሁምን? መኝታ ስፍራችሁን የያዛችሁ ጊዜ ወይም ወደ መኝታችሁ ስፍራ የተጠጋችሁ ጊዜ ሰላሳ ሶስት ጊዜ 'ሱብሓነላህ' ሰላሳ ሶስት ጊዜ 'አልሐምዱሊላህ' ሰላሳ አራት ጊዜ ደግሞ 'አላሁ አክበር' በሉ። ይህም ለናንተ ከአገልጋይ የተሻለ ነው።

ከዓሊ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው: ፋጢማ (ረዲየሏሁ ዐንሃ) - አላህ መልካም ሥራዋን ይውደድላትና - ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ዘንድ በወፍጮ ምክንያት እጇ ላይ ስለሚያጋጥማት ጉዳይ ለማማከር መጣች። እርሳቸው ዘንድ ባሪያ እንደመጣም ወሬ ደረሳት። ቤት ስትሄድም አላገኘቻቸውምና ይህንን
ለዓኢሻ አወሳችላት። እርሳቸው ሲመጡም ዓኢሻ ለርሳቸው ነገረቻቸው። ዓሊይ እንዲህ አለ: «መኝታችን ላይ ሆነን ሳለ መጡ። ለመነሳት ስንዘጋጅም "ባላችሁበት ሁኑ" አሉንና መጥተው የእግራቸው ቅዝቃዜን ሆዴ እስኪሰማው ድረስ በኔና በርሷ መካከል መጥተው ተቀመጡና
እንዲህ አሉ: "ከጠየቃችሁት የተሻለን ነገር አልጠቁማችሁምን? መኝታ ስፍራችሁን የያዛችሁ ጊዜ ወይም ወደ መኝታችሁ ስፍራ የተጠጋችሁ ጊዜ ሰላሳ ሶስት ጊዜ 'ሱብሓነላህ' ሰላሳ ሶስት ጊዜ 'አልሐምዱሊላህ' ሰላሳ አራት ጊዜ ደግሞ 'አላሁ አክበር' በሉ። ይህም ለናንተ ከአገልጋይ የተሻለ ነው።"»
[ሶሒሕ ነው።] [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

የነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ሴት ልጅ የሆነችው ፋጢማ (ረዲየሏሁ ዐንሃ) - አላህ መልካም ሥራዋን ይውደድላትና በወፍጮ ስትፈጭ እጇ ላይ ስለሚደርስባት ምልክት ለነቢዩ ስሞታ አቀረበች። ወደ ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ምርኮኛ የመጣ ጊዜ የቤት ስራን የሚተካላት ከነዚህ ምርኮኞች መካከል አንድ ሰራተኛ እንዲሰጧት ለመጠየቅም ወደርሳቸው ሄደች። ነገር ግን ቤት ውስጥ አላገኘቻቸውም። ዓኢሻን (ረዲየሏሁ ዐንሃ) - አላህ መልካም ሥራዋን ይውደድላትና ስለነበር ያገኘችው ለርሷ ነገረቻት። ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ቤታቸው ሲመጡም ፋጢማ ወደርሳቸው ሰራተኛን ልትጠይቃቸው መጥታ እንደነበር ነገረቻቸው። ነቢዩም (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ፋጢማና ዐሊይ (ረዲየሏሁ ዐንሁማ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና ዘንድ ፍራሻቸው ላይ ለእንቅልፍ እየተዘጋጁ ሳለ ቤታቸው መጡ። ዐሊይ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - ሆዱ ላይ የነቢዩን (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) የእግር ቅዝቃዜ እስኪሰማው ድረስ በመካከላቸው ተቀመጡ። እንዲህም አሏቸው: ሰራተኛን እንድሰጣችሁ ከጠየቃችሁኝ ይልቅ የተሻለውን ነገር አላስተምራችሁምን? እነርሱም: እንዴታ አሏቸው። ነቢዩም (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ አሉ: ምሽት ላይ የእንቅልፋችሁን ስፍራ የያዛችሁ ጊዜ ሰላሳ አራት ጊዜ 'አላሁ አክበር' በሉ። ሰላሳ ሶስት ጊዜ 'ሱብሓነላህ' በሉ። ሰላሳ ሶስት ጊዜም 'አልሐምዱሊላህ' በሉ። እነዚህ ዚክሮች ለናንተ ከሰራተኛም የተሻሉ ናቸው።

http://www.sunnah.global/hadeeth/am/show/6076